የርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረጽዮን ቅድስት ማርያም የኢ/ኦ/ተ/ቤተክርስቲያን
የሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤ

ቀን 30/02/2002 (09/11/09

<u>በስብሰባው የተገኙ አባላት</u>
መሪ/መርሀጽድቅ ቀናው የጉባኤው ሰብሳቢ
ልዑል ሚካኤል መኮንን የጉባኤው አባል
ሊ/ዲ/ ዳዊት ደንበሩ የጉባኤው አባል
ብ/ጀ/ኃይሉ መረዋቅ የጉባኤው ጸሐፊ

<u>አጀንዳ</u>
በየሶስት አመቱ የሚፈጸመው የሰበካው አስተዳደር ጉባኤና የንኡሳን ኮሚቴዎች አባላት ምርጫ ስለሚካሄድበት ሁኔታና እስከአሁን በሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤው በኩል የተፈጸሙትን ተግባራት ገምግሞ ቀጣዩን እርምጃ ለመወሰን ነው።

የሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤ ዋና አላማና ተግባር የቤተክርስቲያናችንን አስተዳደርና አገልግሎት ለማሻሻልና የካህናቱንና የምእመናኑን አንድነት ለማጠናከር ታስቦ በጠቅላላው ጉባኤ ጸድቆ የወጣውን የመተዳደሪያ ህግና ድንብ በሁሉም ዘርፍ እንዲፈጸምና ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ሲሆን በተለይ ስለምርጫ አፈጻጸም የተደነገጉትን ደንቦች በማስፈጸሙ ረገድ ወሳኝ ሚና ያለው ለመሆኑ በዚሁ ህግ አንቀጽ 7 (3መ) በግልጽ ተደንግጓል።

በዚህ መርህ መሰረት የሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤ በጠቅላላው ጉባኤ ተመርጦ ሃላፊነቱን ከተረከበበት ከየካቲት ወር 1999 ዓ.ም (2007) ጀምሮ 24 ቋሚና አስቸኳይ ስብሰባዎችን በማድረግ በህጉ መሰረት መፈጸም አለባቸው በሚላቸውና ከህጉ ውጭ ተፈጽመዋል በሚላቸው ጉዳዮች ላይ በጽሁፍና በቃል (በውይይት) ለሰበካው አስተዳደር ጉባኤውም ሆነ ለሚመለከታቸው ንኡሳን ኮሚቴዎችና የካህናት ጉባኤ መመሪያዎችንና ውሳኔዎችን እንዲሁም ዘላቂ የሆነ የቤተክርስቲያናችንን አንድነትና ሰላም ሊያመጣ የሚችለው ያለንን ህግና ስርአት ተከትለን መስራት ስንችል ብቻ መሆኑን በተደጋጋሚ ሲያስተላልፍና ምክሩን ሲሰጥ ቆይትዋል። የሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤው መመሪያ ፤ ምክርና ውሳኔ ከሰጠባቸው ጉዳዮች ዋናዎቹ ፤

1ኛ. በጠቅላላው ጉባኤ የተቋቋመው አስመራጭ ኮሚቴ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የምግባረ ሰናይ ኮሚቴ አባላት ምርጫን እንዳይካሄድ በመደረጉ ምክንያት የተሰጠ ዝርዝር የህግ ማብራሪያና መመሪያ

2ኛ. የቤተክርስቲያናችን ገንዘብና ንብረት አያያዝ ሀሜትና ጥያቄ በማያስነሳበት ሁኔታ ህጉን ተከትሎ እንዲፈጸም በሚል ፤

3ኛ. የቁጥጥር ኮሚቴው በውስጠ ደንቡ አንቀጽ 28 መሰረት ስራውን እንዲጀምርና የቁጥጥር ሪፖረቱን በየ3 ወሩ ለአስተዳደር ጉባኤውና በየአመቱ ለጠቅላላው ጉባኤ በማቅረብ የተሰጠውን የመቆጣጠር ሃላፊነት እንዲወጣ በሚል ፤

4ኛ. የቤተክርስቲያኑ ዋና ጸሃፊ በህጉ መሰርት ያልተመደበ በመሆኑ ህጉን ተከትሎ እን ዲፈጸም በሚል ፤

5ኛ. በቤተክርስቲያናችን ውስጥ መደረግ ስለሚገባው የጤንነትና የደህንነት ጉዳይ (Health & safety regulations)

6ኛ. በአለፈው አመት በተካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የንብረትና የገንዘብ አያያዙን አስመልክቶ በተነሱት ጥያቄዎች ምክንያት የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ ላስተላለፈው ህጉን ያልተከተለ ውሳኔ በሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤ በኩል የተሰጠ ህጋዊ መመሪያና ምክር ፤

7ኛ. በአስተዳደር ጉባኤውም ሆነ በንኡሳን ኮሚቴዎች የጎደሉ አባላት በህጉ መሰረት ምርጫ ተደርጎ እንዲሞዋሉ በሚል የተላለፉ ናቸው።

የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ ግን ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መመሪያዎችና ውሳኔ ዎች ካለመፈጸሙም ሌላ በሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤ የሚሰጠውን መመሪያና ምክር ሁሉ በቤተክርስቲያን አስተዳደር ውስጥ ፈጽሞ ሊነሳ ከማይገባው የስልጣን ጥያቄ ጋር በማያያዝ ለብዙ ጊዜ ተደክሞበት በጠቅላላው ጉባኤ ጸድቆ የወጣውን ህግና ደንብ

ተግባራዊ እንዳይሆን በማድረጉ በካህናቱም ሆነ በምእመናኑ መካከል የነበረው ሰላምና አንድነት እንዲደበዘዝና የእረስ በእረስ መተማመን እንዳይኖር አድርጎታል።

ይህ በዚህ እንዳለ የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ አባላትም ሆኑ የንኡሳን ኮሚቴዎች አባላት ለተመረጡበት ህግ ተገዢ የማይሆኑ ከሆነ በውስጠ ደንቡ አንቀጽ 48 (1) መሰረት አስፈላጊው የስነስርአት እርምጃ እንድወሰድባቸው ወይም ከሃላፊነታቸው እንዲወረዱና ሌሎች ህጉን አክብረው ሊያገለግሉ የሚችሉ ካህናትና ምእመናን እን ዲመረጡ ለማድረግ የሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤ በአንቀጽ 44 (2ሐ) መሰረት ጠቅላላው ጉባኤ እንዲጠራ አድርጎ ሪፖርት ማቅረብ ሲችልና በሪፖረቱም መሰረት ማናቸውም የቤተክርስቲያናችን አባላት ህጉ ተጣሰ ፤ የቤተክርስቲያኑ ገንዘብና ንብረት በህጉ መሰረት አልተጠበቀም በማለት ለሚመለከተው የውጭ ህጋዊ አካል ጭምር መጠየቅ እንደሚችሉ በግልጽ የተገነዘበው ቢሆንም የእርስ በእርስ መለያየትና መካሰስ በቤተክርስቲያናችን ካህናትና ምእመናን ማህበራዊና መንፈሳዊ ህይወት ላይ የሚያመጣውን አሉታዊ ተጽእኖ አርቆ በማሰብ ማንኛውንም ህጋዊ እርምጃ ከመውሰድ ተቆጥቦና ታግሶ ለሁሉም ተመራጭ አባላት በአንቀጽ 10 እና 37 መሰረት የተወሰነው የሶስት አመት የአገልግሎት ዘመን ሲያልቅ በሰላም አዲስ ምርጫ ማካሄዱ አማራጭ የሌለው መፍትሄ መሆኑን የሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤው አምኖበት እስከአሁን ድረስ የምርጫውን ጊዜ ሲጠባበቅ ቆይትዋል።

ይሁን እንጂ በውስጠ ደንቡ አንቀጽ 6 (12) መሰረት የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ አባላት ምርጫና እንዲሁም የሌሎቹ ንኡሳን ኮሚቴዎች ምርጫ በተከታታይ በግንቦት ወር ጀምሮ ሲሆን እስከአሁን ድረስ የምርጫ ዝግጅት አለመደረጉና ለጠቅላላው ጉባኤም አለመነገሩ ለሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤውም ሆነ ለብዙዎች ካህናትና ምእመናን አሳሳቢ ጉዳይ እየሆነ በመምጣቱ በፖለቲካው አለም የሚታየው ተገቢ ያልሆነ የእርስ በእርስ መለያየትና መካሰስ በቤተክርስቲያናችን ካህናትና ምእመናን መካከል እንዳይታይ ሁሉም ካህናትና ምእመናን አስፈላጊውን ጥረት እንዲያደርጉ የሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤው አጥብቆ ያሳስባል።

ስለዚህ ለሰበካው አስተዳደር ጉባኤም ሆነ በመዋቅሩ ውስጥ ላሉ ኮሚቴዎች በአባልነት ተመርጠው በማገልገል ላይ ያሉ አባላት ሁሉ በቤተክርስቲያን ውስጥ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የተመረጡ መሆናቸውንና ከላይ የተጠቀሰው በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ቢታይ በእምነታችንም ሆነ በአንድነታችን ላይ የሚያስከትለውን አሳፋሪ የሆነ ጸብና ክርክር ተገንዝበው ቢቻል ለሁሉም ካህናትና ምእመናን የእርቀሰላም ጥሪ ተደርጎ ምርጫው በውሰጠ ደንቡ አንቀጽ 7 መሰረት በሰላምና በፍቅር ሊካሄድ የሚችልበት ሁኔታ እንዲመቻች የሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤው አጥብቆ ይጠይቃል።

ነገር ግን አሁንም በሀገራችን እንደምናየው የሃይማኖታችንን መርህ በመዘንጋትና የሌሎች ካህናትንና ምእመናንን መብት በመጋፋት እንዲሁም የህግ የበላይነትን ባለማክበርና ለጠቅላላው ጉባኤ አባላት ተጠያቂነትንና ተጠሪነትን ዘንግቶ ህጋዊ ያልሆነ ምክንያት በመፍጠር ምርጫው በወቅቱ የማይደረግ ከሆነ ላለፈውም ሆነ ለወደፊት በቤተክርስቲያኑ ገንዘብና ንብረት (የህዝብ ገንዘብ) ፤ እንዲሁም በካህናቱና በምእመናኑ አንድነትና ሰላም ላይም ሆነ ከላይ እንደተገለጸው በውጭው ህጋዊ አካል እስከመካሰስ ለሚደርሰው ችግር ሁሉ ተጠያቂዎቹ በግልም ሆነ በጋራ የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ አባላት መሆናቸውን በድጋሜ እያስጠነቀቀ ይህ የሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤ ስራውን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ህጉንና ስርአቱን ለማስከበርና የቤተክርስቲያኑ ሃብትና ንብረት በተገቢው መንገድ እንዲያዝና እንዲጠበቅ ያደረገውን ጥረትና የተፈጸሙትን ችግሮች በመዘርዘር ሃላፊነቱን ለሰጡት ለጠቅላላው ጉባኤ አባላት በማሳወቅ የበኩሉን ሃላፊነት እንደሚያስረክብ በአንድ ድምጽ ተስማምቶ ወስንዋል።

ይህ ቃለጉባኤ ለቤተክርስቲያኑ ጽ/ቤት በሸኝ ደብዳቤ እንዲደርስ ሆኖ ኮፒው/ግልባጩ ለእያንዳን ዱ የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ ፤ የካህናት ጉባኤ ፤ የንኡሳን ኮሚቴዎች አባላት እንዲሁም ለጠቅላላው ጉባኤ አባላት እንዲደርሳቸው በሚል ጉባኤው ተስማመቶ የስብሰባው ፍጻሜ ሆኖአል።